# ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ምን እንደሚያካትት

እርስዎንም ጨምሮ፣ የእርስዎ ልጅ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ስብሰባ ሲያደርግ፣ ስለ እርስዎ ልጅ ወቅታዊ የማሻሻል-እርምጃ ለመመልከት እና ልጅዎ እንዴት ከሪኩለም ለማግኘት እንደሚችል/እንደምትችል፣ ቡድኑ IEP ይፈጥራል። በእርስዎ ልጅ IEP ገጾች ላይ ከተገለጸው ይዘት ጋር ተመሣሣይነት ያለው የ IEP ማብራሪያ በአጭሩ እዚህ ይገኛል። ተመሣሣይ የ IEP ገጾችን ለማየት ከዚህ በታች ያለውን ቅጥያ/አገናኝ/hyperlinks ጠቅ ያድርጉ።

## የተማሪ እና የትምህርት ቤት መረጃ/ኢንፎርሜሽን

ከአስፈላጊ የስነ ሕዝብ/ባህሪያት መገለጫ መረጃ/ኢንፎርሜሽን በተጨማሪ፣ በዚህ ገጽ ላይ የእርስዎን ልጅ ጉዳይ የሚከታተል/የምትከታተል ማናጀር ስም፣ አገልግሎት የሚሰጥበትን ትምህርት ቤት (የእርስዎ ልጅ የልዩ ትምህርት አገልግሎት የሚያገኝበትን/የምታገኝበትን ቦታ)፣ የእርስዎ ልጅ ያለበ(ባ)ትን ተቀዳሚ ስንክልና፣ እና በመማሪያ ክፍል ውስጥ እንዴት አይነት ተጽእኖ ሊያሳድርበ(ባ)ት እንደሚችል ያገኛሉ። ስላለፉት እና ስለመጪዎቹ የ IEP ቡድን የስብሰባ ቀናት እና ስብሰባ የተካፈሉ የሁሉም አባላት ዝርዝር አስፈላጊ መረጃ በዚህ ገጽ ላይ ይገኛል።

## የመጀመሪያ ብቁነት

ይህኛው የ IEP ገጽ የእርስዎ ልጅ የመጀመሪያ ቀን ብቁ መሆኑን/መሆኗን (የመነሻ ብቁነት) የአካል ስንክልና ኮድ እና በመነሻ ለምን/እንዴት የእርስዎ ልጅ ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ ሆኖ እንደተገኘ/ች የሚገልጽ ኢንፎርሜሽን አለው። የእርስዎ ልጅ ቅድመ ት/ቤት - ወይም በትምህርት ቤት ዕድሜ ላይ መሆኑ/ኗ ላይ በመመስረት ይህኛው ገጽ የተለየ ይሆናል።

## ቀጣይ ብቁነት

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የልጅዎን ብቁ የመሆን አቋም ቢያንስ በሦስት ዓመት አንድ ጊዜ እንደገና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት (በድጋሚ ግምገማ ማድረግ)። በዚህ ገጽ ላይ ስለ ስንክልና ኮድ፣ የእርስዎ ልጅ ለልዩ ትምህርት ብቁ በመሆን የሚቀጥልበትን/የምትቀጥልበትን ምክንያት(ቶች) ጭምር፣ስለብቃት መስፈርት ድጋሚ ግምገማ የተደረገበትን የመጨረሻ ቀን ያንፀባርቃል።

## ዲስትሪክት/ስቴት አቀፍ ግምገማዎች ላይ ስለ መሣተፍ እና የመመረቂያ መረጃ/ኢንፎርሜሽን

በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት ድንጋጌ መሠረት፣ ፈተና/ግምገማ የመጨሰድ ደረጃዎች ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ በመደበኛ ወይም በአማራጭ/ተለዋጭ ፈተና/ግምገማ/assessment ላይ መሣተፍ ይኖርባቸዋል። በዚህ ገጽ ላይ የእርስዎ ልጅ በአማራጭ/ተለዋጭ የትምህርት ማዕቀፍ (የተማሪን ሁኔታ/ፍላጎት በመመርኮዝ ተሻሽሎ የተዘጋጀ ከሪኩለም)ተለዋጭ ግምገማዎች/ፈተናዎች/assessments መሣተፍ ይኖርበ(ባ)ት እንደሆነ ይገልጻል። ለዚህ ውሳኔ የእርስዎ ስምምነት/ፈቃድ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪ፣ ይኼኛው ገጽ የእርስዎ ልጅ የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ወይም የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የፕሮግራም ማጠናቀቂያ ሠርተፊኬት ያገኝ/ታገኝ እንደሆነ ያለውን ኢንፎርሜሽን ይገልጻል። ለዚህ ውሳኔ የእርስዎ ስምምነት/ፈቃድ አስፈላጊ ነው።

## የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ብቃት ማጠቃለያ እና ስቴት አቀፍ የድርጊት/አፈጻጸም ማጠቃለያ

የእርስዎ ልጅ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ (ELL) ከሆነ/ች ይህኛው መረጃ (ኢንፎርሜሽን) በዚህ ገፅ ላይ ይጨመራል። በተጨማሪም፣ ስለ እርስዎ ልጅ ወቅታዊ የፈተና ውጤት ማጠቃለያ ያገኛሉ/ይደርስዎታል።

## ወቅታዊው የአካዳሚክ ስኬት እና የተግባር አፈፃፀም ደረጃዎች

ይኼኛው "present levels" የተሰኘ የ IEP ክፍል ልጅዎ በአሁኑ ወቅት በትምህርት ቤት እንዴት እየሠራ(ች) እንደሆነ ወይም የልጅዎ አካለ ስንኩልነት በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚሠራው/ለምትሠራው ሥራ ምን ዓይነት ተፅእኖ እንደፈጠረ ለማወቅ ለሚኖርዎት ጥያቄ መልስ የሚያገኙበት ክፍል ነው። "present levels" የሚያካትተው የእርስዎን ልጅ ጥንካሬዎች እና ፍላጎቶች፣ እንዲሁም የእርስዎን አስተዋፅኦ/ግባት፣ የ MCPS ቅጽ 336-39 ጨምሮ ከተለያዩ ምንጮች በተገኘ መረጃ/ኢንፎርሜሽን መሠረት የወላጅ ሪፖርት፣ ወይም ጠንካራ ጎኖች እና የፍላጎቶች ማጠቃለያ፡- A Look at My Child's Development for preschool. የእርስዎ ልጅ በቅድመ ት/ቤት -ወይም የት/ቤት-እድሜ ከሆነ(ች) የአሁን ደረጃ የተለየ ሊሆን ይችላል።

## ልዩ ትኩረት የሚሰጥባቸው ነገሮች

ባለው ወቅታዊ መረጃ እና በልጅዎ ግላዊ ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ ምናልባት የእርስዎ ልጅ ተጨማሪ የድጋፍ አይነት የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት ልዩ ሁኔታ ካለ የ IEP ቡድኖች እርምጃ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። (አግባብ በሚሆንበት ቦታ) የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- መገናኛ
- እውር/የማየት ስንክልና
- መስማት የተሳናቸው/የመስማት ችግር ያላቸው (Deaf/Hard of Hearing)
- ስነምግባራዊ
- ELL

ይቀጥላል

## የማስተማር እና የፈተና መገልገያዎች

ተማሪዎች የአካል ስንክልና ያለባቸውበስቴት ወይም ዲስትሪክት አቀፍ ምዘናዎች ላይ መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል። ለእርስዎ ልጅ ቴስት በሚደረግበት/በምትደረግበት ወቅት መገልገያዎች/accommodations ወይም ሌላ አይነት መመዘኛ ያስፈልግ እንደሆነ የ IEP ቡድን መወሰን አለበት። በዚህኛው ክፍል፣ የእርስዎ ልጅ እንዴት እንደሚሳተፍ/እንደምትሳተፍ እና ቴስት በሚደረግበት/በምትደረግበት ወቅት ምን አይነት ድጋፎች መስጠት እንደሚያስፈልግ የ IEP ቡድን ይመዘግባል። በተለይም፣ ቴስት በሚደረጉበት ወቅት የሚሰጣቸው መገልገያዎች/accommodations መጀመሪያ በመማሪያ ክፍል ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ መሰጠት አለባቸው። ሦስት አይነት መገልገያዎች/አኮመደሽን አሉ:-

- የአቀራረብ መገልገያዎች/አኮመደሽን:- መረጃ/ኢንፎርሜሽን እንዴት እንደሚቀርብ
- የግብረመልስ መገልገያዎች/አኮመደሽን:- በምን መልኩ ተማሪ ምላሽ የሚ(ምት)ሰጥበት
- የጊዜ መገልገያዎች/አኮመደሽን:- የተማሪ የግብረመልስ ጊዜ

## ተጨማሪ ድጋፎች እና አገልግሎቶች

ተጨማሪ ድጋፎች እና አገልግሎቶች ልጅዎ በትምህርት እና በመላው አካዴሚያዊ፣ ከከሪኩለም በተጨማሪ፣ እና አካደሚያዊ ባልሆኑ እንቅስቃሴዎች እና መሰናዶዎች የመማር እና ተሳትፎ እንዲኖረው/ራት ታስቦ የተነደፈ ነው። የማስተማር ድጋፎች፣ ፕሮግራም ማሻሻያዎች፣ ማህበራዊ/ስነምግባር ድጋፎች፣ አካላዊ/የአካባቢ ድጋፎች፣ እና የትምህርት ቤት ሠራተኞች/የወላጆች ድጋፎችን ያካትታል።

## የተራዘመ የትምህርት አመት (ESY)

ESY የተዘጋጀው በ IEP የተካተተውን እና መደበኛ ትምህርት ቤት ከተዘጋ በኋላ ሰመር ላይ ለሚሰጠው የተለየ ዓላማ ግብ እንዲደርስ/እንድትደርስ ለማስቻል የእርስዎን ልጅ ለመርዳት የተነደፈ ነው። የእርስዎ ልጅ ለ ESY አገልግሎቶች ብቁ መሆን ይችል/ትችል እንደሆነ እና ምን መመዘኛ-መስፈርት ማሟላት እንደሚገባ ይህ ገጽ ለይቶ ይዘረዝራል።

## የሽግግር እቅድ

የእርስዎ ልጅ ወደ 14 ዓመት እድሜ ሲሸጋገር ከሚጀምረዉ የIEP ዓመት በፊት ጀምሮ ፣የእርስዎ ልጅ ከተመረቀ/ች ወይም የሠርተፊኬት ፕሮግራም ካጠናቀቀ/ች በኋላ ህይወት ለመምራት ለማዘጋጀት ለመርዳት የተነደፈ IEP የሽግግር ግቦች፣ አገልግሎቶች፣እና እንቅስቃሴዎች እንዲኖረው ያስፈልጋል።

በተደረገላቸዉ ቃለመጠይቅ በልጅዎ ምርጫዎች መሰረት ይህ የሽግግር እቅድ ልጅዎ ለኮሌጅ እና ለስራ ዝግጁ እንዲሆን/እንድትሆን ያግዛል።

## ዓመታዊ ግቦች

አንዴ የልጁ/ጅቷ ፍላጎቶች ከታወቁ በኋላ የ IEP ቡድን እነዚያን ፍላጎቶች ለማሟላት የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው ግቦችን ያዘጋጃል። ይህ ገጽ የሚያካትተውዓመታዊ ግቦችን፣ የእርስዎ ልጅ በአንድ ዓመት IEP ቆይታ ምን ለማድረግ ወይም ለመማር እንደሚጠበቅበ(ባ)ት ያካትታል። የአጭር-ጊዜ ዓላማዎች እና መለኪያዎች የእርስዎ ልጅ አሁን ካለው/ካላት አሠራር በዓመት ግብ የደረሰበትን/የደረሰችበትን ትርጉም ያለው የመካከለኛ ጊዜ ውጤቶች ይገልጻል። የእርስዎ ልጅ IEP ዓመታዊ ግቦችን ለመድረስ የሚያደርገውን/የምታደርገውን እርምጃ እንዴት መለካት እንደሚቻል፣ መቼ ለእርስዎ እንደሚገለጽ፣ እና ዓመታዊ ግብ ለመምታት ልጅዎ ምን ያክል እርምጃ እንዳሳየ/ች በተጨማሪ ይገልጻል።

## አገልግሎት መስጠት

በ "services page" ላይ .. በሚመለከት ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች መልስ ያገኛሉ:-

- የእርስዎ ልጅ ምን አይነት አገልግሎቶችን ያገኛል/ታገኛለች?
- የእርስዎ ልጅ አገልግሎት ማግኘት የሚጀምረው/የምትጀምረው መቼ ነው?
- አገልግሎቶች የሚሰጡት የት ነው?
- አገልግሎቶች የሚሰጡት በምን ያክል ጊዜ ይሆናል?
- "ክፍለ ጊዜው" ምን ያክል ጊዜ ይወስዳል?
- አገልግሎት የሚሰጠው ማነው?

## አነስተኛ ገደብ ያለበት አካባቢ/ሁኔታ (LRE)

በዚህ ገጽ ላይ:- ስለ ምደባ ውሳኔ (የእርስዎ ልጅ የት አገልግሎቶችን እንደሚያገኝ/እንደምታገኝ) እና LRE የእርስዎ ልጅ የአካል ጉዳተኝነት ከሌላቸው እኩዮቻቸው ጋር በጣም ተስማሚ በሆነ የት ቦታ እንደሚማር/እንደምትማር ዝርዝር ይገልጻል። የአካል ጉዳት ከሌላቸው እኩዮች ጋር የሚሰጡት አገልግሎቶች ተስማሚ ካልሆነ፣ ድጋፍ እየተሰጠ እንኳ በመደበኛ የትምህርት ማእቀፍ ለምን አገልግሎቶችን መስጠት ተስማሚ ሊሆን እንዳልተቻለ ጭምር ቡድኑ ሌሎች አማራጮችን ለይቶ ይመዘግባል። ይኼኛው ገጽ ደግሞ ለእርስዎ ልጅ ልዩ አይነት መጓጓዣ (የልዩ ትምህርት ቤት አውቶቡስ) ያስፈልግ እንደሆነ ይገልጻል።

## ፈቃድ

ለእርስዎ ልጅ የመጀመሪያ IEP እና የልዩ ትምህርት ተነሣሽነት እና/ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶችን በሚመለከት የእርስዎን ስምምነት ማረጋገጫ የሚሰጡበት ገጽ ነው (በሜሪላንድ ህግ መሠረት ከመጀመሪያው IEP በኋላ የእርስዎ ስምምነት አስፈላጊ አይሆንም)።

## የህክምና እርዳታ

ይኼኛው ገጽ የሚሠራው በ Medicaid አማካይነት የህክምና እርዳታ ለሚያገኙ የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ብቻ ነው። በፊርማዎ፣ ለልጅዎ በተሰጡት አገልግሎቶች MCPS ከ Medicaid የክፍያ መጠየቂያ/bill እንዲያስከፍል መፍቀድዎን ያረጋግጣሉ።